# ***የሁለቱ ጩኸቶች ልዩነት***

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*

## ***የማያስደነግጥ ጩኸትና : የሚያስደነግጥ ጩኸት፤***

*ሁለቱንም ጩኸቶች፤ ከነ ምክንያትና ውጤቶቻቸው (Cause and effect) ጋር፤ ማን ? በማን ላይ ጩኸ ? የት ? መቼ ? ለምን ? እንዴት ? ውጤቱስ ? የሚሉ ጥያቄዎች እያነሳን እናስተውላቸው፤*

*ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም « አንገት ሲደፋ ምን ፈሰሰ? » በሚል ጸሁፋቸው እንዳሉት፤ በኛ 1928-29ዓ.ም. እኤአ ሰኔ1936 በጀኔቫ፤ በወቅቱ « ሊግ ኦፍ ኔሽንስ (League of Nations) » የዓለም መንግሥታት ማህበር ተብሎ ይጠራ በነበረው ስብሰባ ላይ አፄ ኃይለሥላሤ ንግግር ባደረጉበት ወቅት የፋሽስት ሙሶሎኒ ተከታዮች፤ በንጉሡ ላይ፤ መጬሃቸው አይካድም ። ለምን? ብለን ብንጠይቅ፤ ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የነሰነሱት መርዛማ የጋዝ ጭስና፤ ያዘነቡት የቦንብ ዝናብ፤ ለዓለም ሕዝብ ጆሮ እንዳይደርስና: ጣሊያን ኢትዮጵያን ቅኝ ተገዢ ለማድረግ ያለመችው ሕልም ዕውን እንዲሆንላቸው ሲሆን፤ ይህ ጩኸት መጠኑ የበረታ ቢሆንም፤ አቶ መለስ ዜናዊ የደነገጡትን ያህል፤ አፄ ኃይለሥላሤ አልደነገጡም፤ ለጥቂት ጊዜ ንግግራቸውን በማቋረጥ፤ ቁልቁል በንቀት ተመልክተው፤ ጥቂት ቃላት ለመግቢያ ያህል በፈረንሳይኛ ቋንቋ ከተናገሩ በኋላ፤ በገዛ ብሔራዊ ቋንቋቸው በዓለም ታሪክ የማይረሳ ንግግራቸውን በመቀጠል፤ የጣልያን ፋሺስቶች በሕዝባቸው ላይ ያደረሱትን ስቃይ በዕውነት ማማ ላይ ቆመው ከመናገራቸውም በላይ፤ «በወቅቱ በኢትዮጵያ የሚነደው እሳት ዓለምን ሁሉ እንደሚለበልብ በትንቢት መልክ አሳሰቡ እንጂ » ደንግጠው አንገታቸውን አልደፉም።*
*ያሉትም ተፈጸመ መላው ዓለም በ 2ኛው የዓለም ጦርነት ተማገደ።*
*በወቅቱም የታይም መጋዚን* (Time Magazine) *የዓመቱ ታላቅ ሰው ብሎ ሰይሟችዋል ።*

*እድሜ ለጀግኖች አያቶቻችንና አባቶቻችን፤ ጣሊያንም ኢትዮጵያን ቅኝ ተገዢ የማድረግ ሕልሟ ቅዠት ሆኖ ቀረ፤ እኛም ነፃነታችን እንደተከበረ ቆየን ። ዛሬ ግን ለመሸጥ እያስማማነው እንገኛለን!*
*እንግዲህ እኔ ይህን የፋሽስቶች ጩኸት **የማያስደነግጥ ጩኸት እለዋለሁ ።***
*ምክንያቱም የጬኹት እራሳቸው ግፍ ፈጻሚዎቹ ፋሺስቶች ሲሆኑ፤ ሳይደናገጡ ሃቁን የተናገሩት አፄ ኃይለሥላሤ ነበሩና ።*

*አበበ ገላው በአሜሪካን አገር በተደረገው የ8ቱ የበለጸጉ አገሮችና የለማኞች የምግብ ዋስትና ስብሰባ ላይ (Alliance for food & neutration Security)፤ አቶ መለስ ዜናዊ 70% of the population ብለው፤ በተውሶ (በነጬች) ቋንቋ ንግግር እንደጀመሩ፤ አበበ ገላው: Meles Zenawi is a Dictator ! አቶ መለስ ዜናዊ አምባገነን ገዢ ናቸው ! ብሎ ሲጬህ ክው ብለው በመደንገጥ አመዳቸው ቦነነ! ቀጠል አርጎም፤ በዚያው እሳቸው በጀመሩት የተውሶ ቋንቋ፤ ምግብ ያለ ነፃነት ዋጋ የለውም ! እስክንድር ነጋን ጨምሮ የህሊና እስረኞች በሙሉ ይፈቱ ! የምንፈልገው ነፃነት ! ነፃነት ! ነፃነት ነው ! ብሎ ሲጬህ፤ ፍጹም ያልጠበቁት ጉዳይ ስለሆነባቸው እንደ ሎጥ ሚስት፤ የጨው ሃውልት ሆነው፤ በመቅረት፤ ተክዘው አንገታቸውን ደፉ።*
***ኢትዮጵያ ግን ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር አንገትዋን አብራ አልደፋችም፤ በፍጹም!***

*ኢትዮጵያ እድሜ ለአድዋና ለማይጨው ጀግኖቿ፤ ለአበበ ቢቂላ፤ በመላው ዓለም ድል ለሚያደረጉ ወንዶችና ሴቶች ሯጬቿ.....ወዘተ ሰንደቅ ዓላማዋ ከፍ ብሎ እየተውለበለበ ለዘላለም ተከብራ ትኖራለች ! በሠሩት ሥራ አንገታቸውን እንደደፉ የሚቀሩት አቶ መለስና ተከታዮቻቸው ብቻ ናቸው! አዎ ብቻ ናቸው !*

*ምነው ፕሮፌሰር መስፍን? ደግሞ ሕዝቡ በምን እዳው ነው ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር አብሮ የሚወቀጠው ?*
*በተራበ፤ በተናቀ፤ በተሰደበ፤ በታሰረ፤ በተፈናቀለ፤ በተሰደደ........ዝርዝሩን ለሕዝብ ትቼዋለሁ ::*
*አቶ መለስ ዜናዊ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያይዟቸውን ክሮች በሙሉ፤ ዕትብታቸው ሳይቀር: ሰንደቅ ዓላማ፤ ድንበር፤ ታሪክ፤ ቋንቋ፤ ባህል፤ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን ጨምሮ፤.........በጣጥሰው ከጣሉ ይኸው 21 ዓመታቸው አለፈ::*

*እስቲ አሁን ደግሞ አቶ መለስ ዜናዊ ለምን ደነገጡ? የሚለውን እናጢን፤*
*አቶ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ፤ ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት አምጥተናል፤ (እነሱ በበሉ ቁጥር የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያገሳው ይመስል)፤ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ተደርጓል፤ ዲሞክራሲ ሰፍኗል፤ ገበሬው ሚሊየነር ሆኗል....ወዘተ እያሉ የውሸት አታሞ እየደለቁ፤ ዛሬም ከ21 ዓመታት በኋላ አሜሪካን ድረስ የመጡት ለዕርዳታና ለልመና አቁማዳቸውን ተሸክመው ከመሆኑም በላይ፤ እንደተለመደው የኢትዮጵያን ለም መሬት ከገበሬው ነጥቀው ለድንበር ዘለል ከበርቴ ለመቸብቸብ ሲሆን፤ በአንፃሩ ሕዝባችን ፈጣሪ ለም መሬትና ውሃ ለግሶት፤ ከራሱ አልፎ ሌላ መመገብ ሲችል፤ ፍትሃዊ የሆነ የመሬት ክፍፍል ስሪትና፤ መልካም አስተዳደር በማጣቱ የተነሳ፤ በኑሮ ውድነት እየተለበለበ፤ በርሃብ አለንጋ እየተገረፈ ይገኛል ::*

*እንግዲህ የአበበ ገላውን ጩኸት ከፋሽስቶቹ ጩኸት የሚለየው፤ ከተበደሉ፤ ከተገፉ፤ ከተራቡ፤ ፍትህ ከተጓደለባቸውና፤ የኑሮ ውድነት ከሚጠብሳቸው፤ ወገኖቹ ጎን በመቆም፤ አድሏዊ፤ ዘረኛ፤ ሙሰኛ፤ ሌቦችና ገዳዮችን በጉያቸው አቅፈው፤ አገር እመራለሁ በሚሉት አቶ መለስ ዜናዊ ላይ የተደረገ ሲሆን፤ ፍትህ የተነፈጉ ዜጎች፤ ፍትህ በነፈጓቸው ላይ ያደረጉት ጩኸት በመሆኑ፤*
***የሚያስደነግጥ ጩኸት እለዋለሁ ::***

*ምንም እንኳን ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም « እኔን ቀልቤን የሳበው፤ አበበ ገላው የተናገረው አይደለም፤ » እንዲሁም « አበበ ገላው የተናገረው እውነት መሆኑንና አለመሆኑን ወደጎን እንተወው » እያሉ በወገርጋራ ቢያልፉትም፤ አበበ ገላው የተናገረው ዕውነት መሆኑን በጽሁፋቸው መጨረሻ ገደማ፤ « በሃያ ዓመት የመሪነት ቦታ ተቀምጠ አንገቱን፤.............በሚል ጀምረው............. በድህነት፤ በችጋር፤ በመረጃ ማነቆ፤ በቴሌቪዥን፤ የዕውቀት ጥበብን ጨምሮ፤ እስከ ኢንተርኔት አገልግሎት ድረስ ያሉትን ችግሮችና አፈናዎች ዘርዝረዋል::*
*ለመረጃ* http://www.quatero.net/pdf/prof-mesfine-fete-190.pdf *ይመልከቱ::*

*ፕሮፌሰር መስፈን፤ ቀጠል አርገው የአቶ ኢሳይያስና የኤርትራውያንን በኒውዮርክ ተሰብስቦ መነጋገር መቻል ጠቅሰው፤ ሁለት ጥያቄዎችን አንስተዋል፤*
*1. ለመሆኑ በኒውዮርክ የኢትዮጵያ ጠ/ሚንስትር ስብሰባ ቢጠራ ስንት ሰዎች ይገኛሉ ?*
*2. ከተገኙትስ ጋር የሰለጠነ ውይይት ማድርግ ይቻላል ? ሲሉ:*

*እውነቱን ለመናገር፤ እሳቸው የሚጠሉንን ያህል፤ እኛ ኢትዮጵያውያን አቶ መለስ ዜናዊን በሰብዕናቸው እንደ ሰው አንጠላቸውም፤ የምንጠላው እመራዋለሁ በሚሉት ሕዝባችንና አገራችን ላይ የሚሠሩትን መጥፎ ተግባር እንጂ:: ፕሮፌሰር መስፍንም « በኢትዮጵያ ውስጥ ተዝናንቶና ኮርቶ ሊያዳምጥ የሚችልበትን መድረክ በሃያ ዓመታት ውስጥ ሳያዘጋጅ መቅረቱ አንገቱን ለመድፋቱ አስተዋጽኦ አድርጓል » ብለዋል::*
*አዎ ! በእጅጉ አድርጓላ ::*
*አሁንም ቢሆን ገና አልመሸም! ግን አቶ መለስ ዜናዊ ዛሬስ ከ 21 ዓመታት በኋላ ለመማር የአይምሯቸውን በር ከፍተዋል?! ወይስ የአእምሮ በርና መስኮታቸውን ክርችም አርድገው ዘግተው ብቻቸውን ............? ምርጫውን ለመራጩ ትተናል!*

*አቶ መለስ ዜናዊ ድፍረቱ የላቸውም እንጂ፤ ቢኖራቸው ኖሮ፤ የዘር ሃረግ ሳይመዙ፤ የፓርቲ ታፔላ ሳይለጥፉ፤ የመከፋፈያ ካራቸውን ሳይወድሩ፤ በፓርላማ እንደተለመደው ጣታቸውን እየቀሰሩ*

*ሳያስፈራሩ፤ በንቀት ሳይወጠሩ፤ ሁሉን አዋቂ ነኝ ሳይሉ፤ በመደጋገም በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ያለውን ሕዝብ ለመከፋፈል መሰሪ ደባቸውን ሳይቋጥሩ፤..........ወዘተ ኢትዮጵያውያንን ጠርተው፤ ኑ ስለአገራችን እንምከር፤ ሠላም እንፍጠር ብለው ሁሉን አቀፍ ስብሰባ ቢጠሩ፤ በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ያሸበረቀ፤ የወጥመድ ድር ያልደራበት፤ አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት፤ በፍቅር፤ በወንድማማችነት፤ በመከባበርና በመደማመጥ ብዙ ሰው ተገኝቶ፤ እጅግ ሰልጡን የሆነ ውይይት ሊደረግ እንደሚችል አልጠራጠርም::*

*ግን ከደረጃ መውጫዎቹ መሃከል የመጀመሪያዋን እግር ማረፊያ ማን ያንጥፋት ?!*

*ሰኔ 7 ቀን 2004 ዓ.ም. (June 14/2012)*